ክፍል አራት

በሰው እንድንጠላ፣የሚያደርግ ዓይነ ጥላ

/ዓይነ ጥላ ጥላቻውን፣በሰው ሲገልጽብን/

በቀሲስ ሄኖክ ወ/ማርያም

ወዳጆቼ በክፍል ሦስት ዓይነ ጥላ ከሰው ጋር እንዳንግባባና በመጨረሻም ትዳር አልባ፣እጮኛ አልባ ብሎም ሰው አልባ አድርጎ ሊያስቀርን እንዴት እንደሚሞክር አይተናል። አሁን ደግሞ በዚህ ክፍል እኛ ላይ እና ሰው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ጥላቸውን በምን ዓይነት የተንኮል ስልት እንደሚዋጋን እናያለን። አምላከ ቅዱሳን ምስጢሩን ይግለጥልን!

ተወዳጆች ሆይ አጋንንት ብዙ ነገራችንን ሊያበላሽ ይችላል። ይህ ደግሞ <<ለምን እና እንዴት>> ብሎ የሚያጨቃጭቀን ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም አሁን ሁላችንም በምድር ላይ የምንኖረው ሕይወት በአጋንንት ቀድሞ በሰማይ ቤት የተበላሸ ሕይወት ነው። በሰማይ ቤት በሰይጣን የተሰበረ ሕይወት ነው በምድር ተሰነጣጥቆ የምንኖረው። በምድር የምንኖረው በእግዚአብሔር ሳይሆን በሰይጣን በኩል የመጣ የውድቀት ኑሮአችንን ነው።

ወዳጆቼ የዓይነ ጥላ አጋንንት በክፋቱ በተንኮሉ በእግዚአብሔር የተጠላ ስለሆነ እኛን እጅጉን ይጠላናል። ዓይነ ጥላ እኛን በሁለት መንገድ በሰዎች ዘንድ እንድንጠላ ያደርገናል። አንደኛው እኛ ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ግንባራችን ላይ፣ዓይናችን ላይ፣ፊታችን ላይ ሆኖ ለሰዎች ፊታችንን በማየት ብቻ አስከፊና የተንኮለኛ ሰው ገጽታን አስመስሎ በማሳየት እንድንጠላ ያደርገናል። ይህ ማለት ሁለት ማንነት ይዘን እንድንታይ ያደረገናል። ደግ ሆነን ንፁግ ሆነን እንድንታይ፤መልካም ሰው ሆነን ክፉ ሰው ሆነን እንድንታይ ያደርገናል። ጨዋ ሆነን ባለጌ ሆነን እንድንታይ ያደርገናል። ለእንደበታችን ለከት ያለን ሆነን ሳለ ወረኛ አድርጎ ለሰው ያሳየናል። ትእግስተኛ ሆነ ሳለ እሳት የላሰ ነገረኛ አድርጎ ያሳየናል፣ሐቀኛ ሆነን ሳለን ከሰው ሙልጭ ያለ ሌባ አድርጎ ያሳየናል። ወዘተ በአንድ ሰውነት ሁለት ማንነትን ይዘን እንድንታይ ያደርገናል። ይህ ሁሉ ዓይነ ጥላው የፊታችንን ገጽታ ለሰው በማሳየት በግምት እንድንጠላ የሚያደርግበት ክፉ ሴራው ነው።

ሁለተኛ ሰዎች ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ያለ ምክንያት ከመፈት ተነስተው ስለ እኛ ምንነት ምንም ሳያውቁ እንዲጠሉን፣በሰዎች ልቡናና ህሊናው ውስጥ ክፉ ሰው እንደሆንን በማሳሰብና የፊት ገጽታችንን ብቻ በማየት እንዲጠሉን ያደርገናል። እኛ ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ሰዎች ከውጭ ሲያዩን ግንባራችንን ብቻ በማየት የክፉ ሰው ምስል ያያሉ ወይም ክፉ ሰው መስለን እንድንታያቸው ያደርጋል። ለእንዳንዱ ደግሞ ከመኮሳተሩ የተነሳ ግንባሩን የተሰበሰበ እና የተከሰከሰ ፊት አድርጎ ያሳየዋል። ለሌሎቹ ደግሞ ነገረኛ እና ተናጋሪ ሰው የሚመስል ምስል ያሳያቸዋል። ሰዎች ቀርበውን ካላዩን በስተቀር እኛ ሁሌም ለሰዎች ክፉ እና መልካምነት የሌለን ይመስላቸዋል። ለዚህም ነው ሰዎች ቀርበው ሲያዩን በውጭ ስለ እኛ ያላቸው አመለካከት በበጎ የሚቀየረው።

ዓይነ ጥላው ይህንን የሚያደርገው የነገን ሕይወታችንን ለማጠየፍ ነው። በተለይ ወንዶች እና ሴቶች በወጣትነት ጊዜያቸው ዓይነ ጥላቸው በእድሜ እኩዮቻቸው ዘንድ እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል። ይህ ደግሞ በነገ በእጮኝነት በትዳር ሕይወታቸው ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድርባቸዋል። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ በሰውነታችን ላይ ለምሳሌ የጥርስ መግጠጥ፣የአይን ፈጠጥ የማለት ነገር ካለ የእኛ እና ሰው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ አግንኖ ለሰው እንድንታይ ያደርገናል። በተለይ በተፈጥሮና ከጊዜ በኃላ በመጣ ምክንያት የቁመና አለመስተካከል ካለብን ለሰዎች እንደተንሻፈፍን፣እንደተንጋደድን አድርጎ ያሳያቸዋል። ሲያዩን አንጥማቸውም።

ወዳጆቼ ሰዎች ሳይሆኑ እነሱ ላይ ያለው ዓይነ ጥላ እንደሆነ የሚጠላችሁ ለማወቅ ለእነዛ ሰዎች ምንም ብታደርጉላቸው፣ውለታ ብትሰሩላቸው፣በችግራቸው ጊዜ ብትደርሱላቸው፣ማንም የማያደርግላቸውን ነገር እንኳን ብታደርጉላቸው ለጊዜው የውሸት ምስጋና ያቀርቡላችኃል እንጂ ውሎ ሳይከርም ጥላቻቸውን ይገልጹላችኃል። ብትሰጡ፣ብታበሉ፣ብታጠቱ አትመሰገኑም። ለሰዎቹ ግዳታችሁ ሁላ ሊመስላቸው ይችላል። ይህ የዓይነ ጥላው ጠባይ <<ውይ ከሰውስ አውሬ ይሻላል>> ብላችሁ ከበጎ ምግባር እናንተን ለማራቅ ይጠቀምባችኃል።

ይህ ብቻ አይደለም እጮኛሞችን ተዋደው ብዙ ነገር ውስጥ ገብተው ሲፋቀሩ ከሁለት ያንዳቸው ዓይነ ጥላ ቀድሞ በፍቅር አይን ዓይቶ ልብ ያላለውን ነገር ለምሳሌ መልክን፣ቁመናን ዳሌን፣ቅንድብን፣ጸጉርን ገልብጦ በመሳየት <<ለካ ይህ ነገርዋ አያምርም፣ለካ ይህ ነገሩ አይማርክም>> እያስባለን የወደድነውን ያፈቀርነውን ሰው እንድንጠላ የጥላቻ ምስሎችን ያሳየናል። ለዚህም ነው በፍቅራቸው የተመሰከረላቸው እጮኛሞች ለእርቅ በማይመች መንገድ የሚጣሉት፣የጀመሩትን የፍቅር ሕይወት ወደ ትዳር ሳይቀይሩት ከመንገድ የሚቀሩት።

ያለ አንዳች ምክንያት በሰዎች ዘንድ የሚጠሉ ሰዎች ሰው ሁሉ የሚወዳቸው ስለማይሰማቸው የዝምታ፣የድብርት፣የጭምተኝነት ባሕርይ ይንጸባረቅብቻዋል።

የራሳችን ዓይነ ጥላ በራሳችን እናት አባት ባንጠላም ከሌሎች ወንድም እህቶቻችን በታች ያለመወደድን ነገር በእኛ ላይ ያሳያል። ዓይነ ጥላው በቤት ውስጥ አንድ ስም ያሰጠንና ሁሌም የመጥፎ ሰው አርአያ ተደርገን እንድናድግ ያደርገናል። በዚህ መልኩ በልጅነት የጠመደን ዓይነ ጥላ ከፍ ስንል ግልጽ ውግያውን በገሀድ ይጀምራል። እኛም ሰዎች እንጂ ዓይነ ጥላው እኛ እንድንጠላ እንዳደረገን ልብ አንልም።

በሰው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ደግሞ በሁለት መንገድ እንድንጠላ ያደርገናል። አንደኛ ሰውዮው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ ሲያየን ደመ ግቡ አንሆንለትም ስለዚህ ይጠላናል። ሁለተኛ ሰው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ እኛ ጋር ያለውን የእግዚአብሔር ጸጋ፣ሞገስ፣የጸሎት በረከት፣ረድኤት እና የተፈጥሮ ጸጋ ለምሳሌ እውቀት፣መግባባት፣ከሰው ጋር ባለን መዋደድ ወዘተ በማየት ይጠላናል። በእነዚህ ስጦታችን የሚጠላን ዓይነ ጥላ እሱ ጠልቶን በሰዎች ዘንድ የበለጠ እንድንጠላ ሰፊ ሥራ ይሠራል። ለምሳሌ ያለ ስም ስም እንዲሰጠን ያደርጋን፣ያልሠራነውን ሠራችሁ ተብለን ጠብ ሊመጣብን ይችላል። ከወንድ ወይም ከሴት ጋር በታየን ቁጥር እንደ ዘማዊ እንድንቆጠርና ዘሙተዋል ብሎ ሊያስወራብን ይችላል።

ሰው ላይ ያለው ዓይነ ጥላ መልካም ንግግራችን ወደ መጥፎ ይቀይራል። መፍትሔ ብለን ሐሳብ ብናፈልቅ <<ኤጭ>> እያለ ጥላቻውን የእኛን ነገር በመናቅ ያሳየናል። በዚህም ከሰው ጋር በፍጹም መግባባት እንደማንችል አድርጎ ሊያሳምነን ይሞክራል። እኛ የምንናገረው ማር የሆነ

ነገር ዓይነ ጥላ ላለበት ሰው ሬት ሆኖ ንግግራችን ይጎመዝዘዋል። በዚህም እኛን በማበሳጨት መልካም ነገሮችን ለማሳጠት ይጠቀምበታል። ይህ የእጮኛሞች እና የባለ ትዳሮች አንዱ ዓይነ ጥላዊ በሽታቸው ነው።

አንዳንድ ሰዎች ለራሳቸው ማወቅ እስኪሳናቸውና የግራ ግራ እስኪገባቸው ድረስ በሰዎች ዘንድ ይጠላሉ። እነሱም የተወዳጁትን ሰው <<ቆይ ግን እኔ ክፉ ነኝ>> እያለ ክፋው ዓይነ ጥላ እንዲጠሉ እንዳደረጋቸው ሳያውቁ ሰውን ይጠይቃሉ። ዓይነ ጥላው ሲከፋብን ሰዎች ገና ቀርበው ባሕርያችንን ሳያውቁ፣ድምጻችንንም በወል ሳይለምዱ ዓይነ ወታችንን በማየት ብቻ ይጠሉናል። ወዳጀቼ በእነዚህ ክስተቶች ዓይን ጥላችንና የሰው ዓይነ ጥላ ነው የጥላቻውን ጥግ የሚያሳን።

አንድ ሴት ወንድየው በስንት ልመና ጓደኛ ካልሆንሽኝ ብሎ ለምኗት እጮኛሞች ይሆናሉ። በጣም ተቀራርበው፣ተላምደው፣ተዋደው ባልታውቀ ምክንያት ይጠላታል ።